# አረጋሽ ለአድዋ--አዎ፤ አረጋሽ ለኢትዮጵያ-- ሞኝህን ብላ

ኢድሪስ አባስ

ሰሞኑን እየታዝብነው ካለው ስንነሳ መጪው የወያኔ የግንቦት ምርጫ የሚካሄደው በውጭ ሃገር በተለይም በአሜሪካ ቢመስለን አይፈረድብንም። የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ከሲያትል እስከ ሳን ሆሴ እየተዘዋወሩ ሰበካ ይዘዋል። ለመሆኑ በባዕድ ሃገር ያሉ ዜጎች--ያውም ዜግነታቸውን የቀየሩ-- በወያኔ ምርጫ ድምጽ ይሰጣሉ? በዚሁ በአሜሪካ ሰሞኑን አንድ ባዕዳንና ኢትዮጵያውያኖች የሚሳተፉብት ጉባኤም ይካሄዳል ተብሏል--አዘጋጆቹና ደጋፊዎቻችው እንደሚሉት ከሆነ ጉባኤው ወያኔን ባይጥለው እንኳን ሳያንገዳግደው አይቀርም-- ምን ይሰማ ጆሮ!

ወደተነሳሁብት ርእስ ስመለስ ደግም አሁንም በባዕድ ሃገር ያሉ ዜጎች የፖለቲካና የሃገራችን ሁኔታ መያዣው መጨበጫው የጠፋቸው ይመስላል። ከቅርብ ጊዘ በፊት ዋና ወያኔ ሆነው ጦርነት ሊስሩብን ሲፎክሩ የነበሩትን፤ ትምክህተኛ እያሉ ያወግዙን የነበሩትን፤ በፈረደበት አማራና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስትጨፍር የነበረችውን ወዘተ ነጻ አውጪያችን ብለው ማሞገሱን ተያይዘውታል። በዚህም መሰረት በየካቲት አብዮት ወቅት አብዮት የተባለው ቡድን አባል ሆኜ(!!) ሳለሁ ቡድኑ ከኢሕአፓ ጋር ሊዋህድ ሲል ኢሕአፓ የብሄረሰቦችን መብት ባለመቀበሉ ከአብዮት ቡድን ወጥቼ ወደ ወያኔ ገባሁ ባይዋን ኣረጋሽን (ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ያካበተውን የፖለቲካ ካፒታል በፍጥነት እያቃጠለ መሆኑ በዚህ መጠቀስ አለበት) ወደ አሜሪካ ጋብዘው ገንዘብም እያዋጡ በመለገስ ላይ ያሉ ግራ የተጋቡ ክፍሎች ከላይ የሰፈረውን --አረጋሽ ለኣድዋ--መፈክርን በየድረ ገጹ ለጥፈዋል። አረጋሽ ለአድዋ? -- አልሰማም አላይን ብዬ ይላል የሃገራችን ኣርሶ ኣደር። መለስን ስታሽንፍ?!!! ችግራችን የሚጀምረው አርጋሽ (ና ስዬ፤ ገብሩ ወዘተ) ለኢትዮጵያ ቆመዋል ወይም ነጻ አውጪያችን ናቸው ሲባል ነው። ማ ቢወልድ ማ! አግባብ አለው--ዘረኞች ናቸውና።

ወደ ሕዝብ ጎራ የሚመጡትን እጃችንን ከፍተን እንቀበል የሚሉ አሉ። ጥያቄው እውን ወይም በሃቅ የሕዝብን ጎራ ሊደባለቁ ነው ውይስ ሕዝብን ዳግም ሊያታልሉና ጠባብነታችውን በኣዲስ ሊጭኑብን ነው የሚለው ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ነው የአጠፉን ይበሉ ጥያቄ በተደጋጋሚ የተነሳው። ይቅርታ ስለጠየቁ ብቻ ሁሉም ቅሬታ ተጠናቀቀ፤ አለቀ ደቀቀ ተቀበረ ማለት አይደለም። ሞኝ የለም ጎበዝ! ከመለስ ዜናዊ በግል የተጣሉ

ሳይሆኑ ከወያኔ ፖለቲካ ጋር ይተቆራርጡ ከሆኑ እስቲ ይህንኑ ዜና ያብስሩን። እስቲ የወያኔን ገበና ያጋልጡ፤ የወያኔን ወንጀል አጋልጠው ያውግዙ። እስቲ በማያወላዳ መንገድ ከወያኔ ይቆራረጡ። ይህን ሳያደርጉ ቀርቶ በወያኔነታችን እንኮራለን፤ ያጠፋነው የለም፤ አንቀጽ 39 አይነካብን፤ ስለ እስረኞች አታንሱብን ወዘተ ማለትን ከገፉበት ሰዎቹ አሁንም ወያኔ ናቸው ብለን ብንደመድም ትክክል ይሆናል። በሕዝባችን ከተማመንን በቀቢፀ ተስፋ ተሸንፈን፣ ላለፈው ላገደመው አስመሳይ ታጋይ ሰለባ አንሆንም። የጣሊያን ጦር ሃገራችንን በወረረበት ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች ጦር ነቅንቀው እና ፎክረው ሊቋቋሙት ሲነሱ ምዕራባውያን አሹፈው አላግጠው ነበር። አርበኞቹ ግን በድል አድራጊነታቸው ላይ ምንም ጥርጥር አልነበራቸውም። ዛሬ ነጻ አውጪያችን ወያኔዎች ወይም ወያኔ የነበሩና አሁንም ወያኔያዊ እምነት ያላቸው ብቻ ናችው የሚሉ ሽንፈተኞች እነሆ አርጋሽ ወይ ሞት መፈክርና አስሙ ሊሉን ተነስተዋል። አያሳዝንም? የማፈሪያዎች መንጋ እንሆ ከበሮውን ለወያኔ እየደለቀ ወያኔነትን ያልተዉትን ንጻ አውጪ ብሎ አቅፏል። የማፈሪያ መንጋ እነዚህኑ በየመድረኩ ጋባዥ፤ በየፓልቶኩ አዳናቂ ሆኖ በነ ስዬና ገብሩ ታስረው ደብዛቸው የጠፋውን ሁሉ ረስቶና ክዶ ራሱን በማዋረድ ላይ አለ።

አረጋሽ ለኣድዋ? ድሮም ነበረች፤ ነገም ከፈለጓት ትሁንላቸው። አረጋሽ ለኢትዮጵያ? ምነው ሃገር ወዳዱ ሁሉ አለቀ እንዴ? ሽንፈተኞችና ሃፍረተ ቢሶች የበላይ ሆኑ እንዴ? ማፈሪያ አንጃዎች በዙ እንዴ?

ከወያኔነቱ ያልጸዳ መቸም ቢሆን መቸ ከሕዝብ ጎራ አይገባ ነው የሕዝብ መፈክሩ!!!